# ድመቷ እና አይጧ

አንድ ጊዜ በጣም የተራበች ድመት አንዲት ትንሽ አይጥ ወደ ጉድጓዷ ስትገባ ተመለከተች፡፡ በዚህ ጊዜ አይጧን ይዛ ለመብላት ከፍተኛ ፍላጎት አደረባት፡፡ ከዚያ ወደ ጉድጓዱ ቀርባ ተናገረች፡፡

‹‹እንዴት ትንሽ ቆንጆ አይጥ ነሽ! በጣም ታምሪያለሽ፡፡ ከጉድጓዱ ውጪና ወደ እኔ ነይ፤ እኔ ጣፋጭ ብስኩቶች አሉኝ፤›› እያለች በጥሩ ቃላት አባበለቻት፡፡

በዚህ ጊዜ ትንሽዋ አይጥ ለመውጣት ጓጓች፡፡ ይሁን እንጂ የድመቷን የማታለያ ንግግር የሰማችው እናትዋ እንዲህ በማለት አስጠነቀቀቻት፡፡

‹‹ልጄ አርፈሽ ተቀመጪ፡፡ ድመቶች መቼም ለኛ ወዳጅ ሆነው አያውቁም፡፡ ይህቺ ድመትም አንቺን በማታለል ጥቃት ልታደርስብሽ ነው፤›› አለቻት፡፡

ድመቷ በበኩልዋ ተስፋ ሳትቆርጥ ቀጠለች፡፡ ትንሽዋንም አይጥ እንዲህ አለቻት፤ ‹‹ትንሽዋ ቆንጆዬ አይጥ፤ ነይ ወደዚህ ውጪና ይህንን አይብና እነዚህን ጣፋጭ ፍሬዎች ተመልከቺ! ላንቺ የሚሆኑ ናቸው፤›› እያለች አሁንም አባበለቻት፡፡

ትንሽዋ አይጥ ልቧ ተነሳሳ፤ ወደ ውጪ ልትወጣ ቋመጠች፡፡ እናም እናቷን እንደገና ጠየቀቻት፡፡

‹‹እሄዳለሁ እናቴ! ... ልሄድ ነው!››

‹‹ተይ ልጄ፣ እንዳታስቢው፤ እግርሽን እንዳታነሺ፣ እኔ የምልሽን ስሚ፣ ድመቶች ለኛ አደገኞች ናቸው፤›› አለቻት፡፡

‹‹እናቴ ምንም አያደርገኝም፡፡ ትንሽ አይብ ለመቅመስ እፈልጋለሁ፣›› በማለት አይጥዋ በፍጥነት ፈትለክ ብላ ወጣች፡፡ እናቷ ልታስቆማት አልቻለችም፡፡ ስለዚህ እናት በጣም ደነገጠች፤ በእጅጉም አዘነች፡፡

ብዙም ሳይቆይ የትንሽዋ አይጥ ለቅሶና ጩኸት ተሰማ፡፡ ‹‹እናቴ፣ እርጂኝ፡፡ ድመቷ በላችኝ፣›› አለች፡፡

እናትዋ ግን ምንም ማድረግ አልቻለችም፡፡ በሐዘን ልቧ ተሰብሮ አለቀሰች፡፡

አያችሁ ልጆች፤ ይህ ተረት ለወላጆቻችንና ለመምህራን መታዘዝ እና ውሳኔያቸውን ማክበር እንዳለብን ያስተምረናል፡፡ ምክንያቱም እነሱ ሁል ጊዜ ለእኛ ጥሩውን ነገር ስለሚያስቡ እነሱን ችላ ማለት እንደ ትንሽዋ አይጥ ለአደጋ ሊያጋልጠን ይችላል፡፡